# ሰው አይጥፋ ባገር

ትናንት መሬት ጮኸ _ ሰው ቀብሮ በውስጡ
ዛሬ ግን እንዳይጮህ _ በቁም በቅምጡ
ታፍኖ ተቀብሮ _ እንዲበላው ምስጡ
በጉድጓድ ዕስር ቤት _ በቁም ነፍሮ አካሉ
እንደነ ደብተራው _ እንዳበራሽ ያሉ
ብዙ ልደታዎች _ በዬ ቦታው አሉ።

ላንደበት አልባዎች _ ጠበቃ እሚናገር
አረ የሰው ያለህ _ሰው አይጠፋ ባገር
ዕምነትን በአደራ _ ያኖሩበት ቦታ
ሰው አይጥፋ ባገር _ ደግሞ እንደ ልደታ
ሰው ይኑር ዘላለም _ ብዕር የጨበጠ
ዕውነቱን የሚያሳይ _ ሻማ እየቀለጠ።

የልደታን የትናንት ሰቆቃ በተባ ብዕሩ ለተረከልን
ፀሃፍ ለቤልጅግ አሊ የምስጋና በረከት ተሆን ዘንድ
ግንቦት 2001
abraham beyenne